የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE
# OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፶፬
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፬ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No 54
ADDIS ABABA 23th March 2016

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፹፫ /፪ሺ፰ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ገጽ ፰ሺ፱፻፵፫

CONTENTS

Council of Ministers Regulation No.383/2016

Ethiopian Agricultural Research Council and Secretariat Establishment Council o Ministers Regulation......Page 8943

የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፹፫ /፪ሺ፰

## የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና ፴፱ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፹፫/፪ሺ፰” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ “አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓት” ማለት በአገሪቱ ውስጥ በግብርና ምርምር ተግባር የተሰማሩ ተቋማት ስብስብ ነው፤

፪/ “ተቋም” ማለት ግብርና ምርምርን እንዲያካሂድ በሕግ የተፈቀደለት የፌዴራል፣ የክልል ወይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም፣ ወይም መንግስታዊ የልማት

COUNCIL OF MINISTERS RERGULATION No.383/2016

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN AGRICULTURAL RESEARCH COUNCIL AND SECRETARIAT

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Articles 5 and 39 of the Definition of Powers and Duties of Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015.

### PART ONE
### GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the “Ethiopian Agricultural Research Council and Secretariat Establishment Council of Ministers Regulation No. 383/2016”.

**2. Definition**

In this Regulation:

1/ “National Agricultural Research System” means a collection of institutions engaged in the agricultural research within the country;

2/ “institution” means a federal, regional or higher education institution, or public or private enterprise authorized by law to conduct agricultural research activities;

ወይም የግል ድርጅት ነው፤



፫/ “ግብርና ምርምር” ማለት በዕፅዋት፣ በእንስሳት እና በተፈጥሮ ሀብት መስክ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚከናወን ምርምር ነው፤

፬/ “የተፈጥሮ ሀብት” ማለት አፈርን፣ ደንን እና ከግብርና ጋር የተዛመደ ውሃን የሚያጠቃልል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት

### ፫. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል::

፪/ የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

### ፬. ዓላማ

የምክር ቤቱ ዓላማ ቅንጅትና የምርምር ትብብር በመፍጠር የግብርና ምርምር ሥርዓቱ ቴክኖሎጂና ዕውቀት በማቅረብ ለሀገሪቱ ፈጣንና ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችል አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓትን ማስተባበር፣ መምራት፣ አቅጣጫ ማስያዝ እና አቅም መገንባት ይሆናል፡፡

### ፭. የምክር ቤቱ አባላት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩/በመንግሥት የሚሰየም…………………….…ሰብሳቢ፣

፪/ የእርሻ እና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሚኒስትር ……………………………………………………አባል፣

፫/ የእንስሳት እና የዓሳ ኃብት ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር……………………………አባል፣

፬/ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ሚኒስትር…………………....አባል፣

፭/ የክልል የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ኃላፊዎች……………………………….....አባል፣

3/ “agricultural research” means a research undertaking to advance production and productivity in the areas of plants, animals and natural resources;

4/ “natural resource” includes soil, forestry and water related to agriculture.

## PART TWO
## ETHIOPIAN AGRICULTURAL RESEARCH COUNCIL

### 3. Establishment

1/The Ethiopian Agricultural Research Council (in this Regulation referred to as “the Council”) is hereby established.

2/ The Council shall be accountable to the Prime Minister.

### 4. Objective

The objective of the Council shall be to coordinate, lead, set directions and build capacity of the national agricultural research system by fostering partnership and collaborative research to enable the research system to avail agricultural technologies and knowledge that would contribute for rapid and sustainable economic development of the country.

### 5. Members of the Council

The Council shall have the following members:

1/ a Government appointee……………..…Chairperson

2/ the Minister of Agriculture and Natural Resources Ministry……………….………..……...member

3/ the Minister of Livestock and Fishery Resources Ministry………………….………………...member

4/ the Minister of Environment, Forestry and Climate Change Ministry……………………....….member

5/ Heads of Regional Agriculture and Natural Resources Bureau ……………………………..……….….member

፮/ የክልል እንስሳትና ዓሣ ሀብት ቢሮ ኃላፊዎች……………………………………....አባል፣

፯/ የክልል አርብቶ አደር ልማት ቢሮ ኃላፊዎች ………………………......................አባል፣

፰/ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር……………………………….……አባል፣

፱/ የክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቶች ዋና ዳይሬክተሮች……………………………....አባል፣

፲/ የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር…አባል፣

፲፩/ የግብርና ምርምር ከሚያካሄዱ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በክላስተር ደረጃ የሚወከሉ ሰባት የምርምር ምክትል ፕሬዚዳንቶች …………………….…...አባል፣

፲፪/ የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን የምርምር ዳይሬክተር……………………………………አባል፣

፲፫/ ሌሎች የግብርና ምርምርን የሚያከናውኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶችና የግል ድርጅቶች አንድ ተወካይ ………………….……………………..…….አባል።

**፮. <u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡

፩/ የግብርና ምርምር በአገራዊ የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ በመመርኮዝ ሳይንሳዊ ይዘቱን ጠብቆ እንዲካሄድ አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቱን አቅጣጫ ማስያዝ፣ መደገፍ፣ ማስተባበር እና መምራት፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የግብርና ምርምርን የሚያካሂዱ ተቋማት ተቀናጅተውና ተናበው የግብርና ቴክኖሎጂ የማቅረብ

6/ Heads of Regional Livestock and Fisheries Bureau …………………………………………….member

7/ Heads of Regional Pastoralist Development Bureau…………………………….…………member

8/ the Director General of Ethiopian Agricultural Research Institute …………………….….…member

9/ Director Generals of Regional Agricultural Research Institutes…………………...……member

10/ Director General of Ethiopian Environment and Forest Research Institute ……………..……..member

11/ seven research vice-presidents represented at cluster level from the higher education institutes engaged in agricultural research activities …………………………………………..…..member

12/ a Research Director of Ethiopian Sugar Corporation……………………….……..member

13/ a representative from other private and public enterprises engaged in agricultural research activities………………………………….member

**6. <u>Powers and Duties of the Council</u>**

The Council may have the following powers and duties:

1/ set directions, support, coordinate and lead the national agricultural research system to undertake agricultural research by maintaining its scientific content in line with the national development policy and strategy;

2/ without prejudice to sub-article (1) of this Article, the Council shall have the following powers and duties:

a) coordinate and lead agricultural research institutions to enable them fulfill their responsibilities of

ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማስተባበርና መምራት፤

፰ሺ፱፻፵፮

ለ) የግብርና ምርምር ፖሊሲን በሚመለከቱ ጉዳዮች መንግስትን ማማከር፤

ሐ) የአገራችንን የቴክኖሎጂ ፍላጎት መሠረት በማድረግ የምርምር ተቋማት ለምርምር አስፈላጊ የሆነ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና ዘመናዊ የምርምር መሠረተ ልማት እንዲያደራጁ ድጋፍ ማድረግ፤ የማበረታቻና የሽልማት ሥርዓት መዘርጋት፤

መ) የምርምር መሣሪያዎች የዓለም አቀፍ ሳይንሳዊ ደረጃን የጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ ውጤታማና ብቃት ያለው የግዥ፣ የተከላ፣ የካሊብሬሽን፣ የፍተሻ፤ የጥገና እና የአወጋገድ ሥርዓት ማስፈን፤

ሠ) የምርምር መሠረተ ልማቶችን ውጤታማነት ለማሳደግ አገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቱ በቅንጅትና በጋራ የሚጠቀሙበትን ሥርዓት መዘርጋት፤

ረ) የግብርና ምርምር ፕሮግራሞች ከአገራዊ የልማት ዕቅድና ስትራቴጂ ጋር ተገናዝበው እንዲዘጋጁ ማድረግ እና ቅደም ተከተልም ማስያዝ፤

ሰ) የምርምር ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች የአገሪቱን የቴክኖሎጂ ፍላጎት በማማከል ሳይንሳዊ ይዘታቸውን ጠብቀው በቅንጅትና በትብብር እንዲተገበሩ ድጋፍ መስጠት፣ የተመረጡና በቅንጅት የሚተገበሩ የምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በበጀት እንዲደገፉ ማድረግ፣ መከታተል፣ መገምገም፣ ማጽደቅ፤

ሸ) በግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት ለሚቀርቡ የተሻሻሉ የሰብል እና የእንስሳት ዝርያዎች፣ ዕውቀቶች እና ሌሎች የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች የመነሻ ብዜትን እና የቴክኖሎጂ ፍላጎት የሚፈጠርበትን ሥርዓት መዘርጋት፤

ቀ) በምርምር ሥርዓቱ ያለውን የሰው ኃይል ለስራ

delivering agricultural technologies in collaboration and partnership;

b) advise the Government in respect of matters related to agricultural research policy;

c) support national agricultural research institutions to build their skilled manpower and state of the art research infrastructure based on the technology needs of the country; lay down incentive and reward system;

d) establish an efficient and effective system for procurement, installation, calibration, testing, repair and disposal of research equipment in conformity with international scientific standards;

e) establish a system whereby national agricultural research institutions undertake their research in a coordinated and integrated manner to promote the efficiency research infrastructures;

f) cause the alignment of agricultural research programs with the national development plan and strategy and set priorities accordingly;

g) provide support to research programs and projects to implement them in a coordinated and integrated manner with due attention to the country's technological demands without losing their scientific contents and provide budgetary support to selected programs and projects being implemented in a coordinated and integrated manner, and monitor, evaluate and approve same;

h) develop a system for demand creation for breeder seed and animal varieties, knowledge and other improved agricultural technology products generated by the agricultural research system;

i) establish performance based motivation and retention system to motivate and retain manpower

ለማነሳሳትና ጠብቆ ለማቆየት የሚያስችል በውጤት ላይ የተመረኮዘ የማበረታቻና የማቆያ ሥርዓት መዘርጋት፤

በ) የግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላትን የምርምር አቅም ለመገንባት የሚገኝ ፋይናንስን በውጤታማነት መጠቀም የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፡፡

**፯. <u>የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር</u>**

፩/ የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ሴክሬታሪያቱን በበላይነት ይመራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምክር ቤቱ ሰብሳቢ፤

ሀ) የምክር ቤቱን መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ በሰብሳቢነት ይመራል፤

ለ) የሴክሬታሪያቱን የምርምር ዘርፍ አስተባባሪ ዕጩዎችን ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

**፰. <u>የምክር ቤቱ ስብሰባ</u>**

፩/ ምክር ቤቱ በሰብሳቢው ሲጠራ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤

፫ የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>የግብርና ምርምር ሴክሬታሪያት</u>

**፱. <u>መቋቋም</u>**

፩/ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ሴክሬታሪያት (ከዚህ በኋላ "ሴክሬታሪያት" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት

in the national agricultural research system;

j) establish a system that enables efficient utilization of funds secured to build research capacity of the organs of the agricultural research system;

**7. <u>Powers and Duties of Chairperson of the Council</u>**

1/ The Chairperson of the Council shall oversee the secretariat.

2/ Without prejudice to the provision of sub-article (1) of this Article, the Chairperson shall:

a) summon and preside over regular and emergency meetings of the Council;

b) Nominate candidates for positions of research sector coordinators of the Secretariat; submit the same for approval by the Council

**8. <u>Meetings of the Council</u>**

1/ The Council shall hold meetings at any time when called by the Chairperson.

2/ There shall be a quorum when more than half of the members are present.

3/ Decisions of the Council shall be passed by majority vote; however, in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ The Council may, without prejudice to the provisions of this Article, adopt its own rules of procedure.

## <u>PART THREE</u>
## <u>AGRICULTURAL RESEARCH SECRETARIAT</u>

**9. <u>Establishment</u>**

1/ The Ethiopian Agricultural Research Secretariat (in this Regulation referred to as the "Secretariat") is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል::



፪ የሴክሬታሪያቱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

**፲. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>**

የሴክሬታሪያቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሎች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሊኖረው ይችላል።

**፲፩. <u>የሴክሬታሪያቱ ስልጣንና ተግባር</u>**

ሴክሬታሪያቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ ከምክር ቤቱ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት የግብርና ምርምርን በመደጋገፍ፣ በመቀናጀት እና በመናበብ በውጤታማነት እንዲያካሄዱ አቅማቸውን ይገነባል፤ ይደግፋል፤ ያስተባብራል፤

፪ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሴክሬታሪያቱ:-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯(፪) የተመለከቱትን የምክር ቤቱን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ በማዋል ረገድ ለምክር ቤቱ ድጋፍ ይሰጣል፤

ለ) የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፤

ሐ) የግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት ተቋማዊ የምርምር አፈጻጸምን መገምገም፣ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት፣ ግብረመልስ መስጠት፤ ተጠሪ ለሆነበት መስሪያ ቤት ሪፖርት ያቀርባል፤

መ) ከምርምር ሥርዓቱ ለወጡ ቴክኖሎጂዎች፤ ዕውቀት፤ አሰራሮችና ኢንፎርሜሽን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአዕምሮአዊ ንብረት መብት ባለቤትነትን እንዲያገኙ አስፈላጊውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

ሠ) የግብርና ምርምር ማዕከላትን አቅም ግንባታ መደገፍ፣ የብቃት ደረጃ የመለኪያ መስፈርት

2/ The Secretariat shall be accountable to the Prime Minister.

**10. <u>Head Office</u>**

The Secretariat shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices in the regions, as may be necessary.

**11. <u>Powers and Duties of the Secretariat</u>**

The Secretariat shall have the following powers and duties:

1/ build capacity, support and coordinate the organs of the agricultural system in accordance with the direction set by the Council to efficiently carryout agricultural research activities through partnership, collaboration and in consultation with each other;

2/ Without prejudice to the generality of the provision of sub-article (1) of this Article the Secretariat shall:

a) provide support to the Council so as to discharge its powers and duties specified under Article 6(2) of this Regulation;

b) serve as Secretariat of the Council;

c) monitor and evaluate research undertakings of the national agricultural system constituents, prepare report, provide feedback and submit report to the body to which it is accountable;

d) create conducive condition, as may be necessary, for the acquisition of ownership of intellectual property rights for technologies, knowledge, process and information generated from the national agricultural research system;

e) support capacity building of agricultural research centers; develop criteria for assessing competence of same; and evaluate and accredit as centers of

ያዘጋጃል፣ በመስፈርቱ መሠረት ይገመግማል፣
፳ሺ፱፻፺፱ የሚሉም የልቀት ማዕከልነት ዕውቅና ይሰጣል፤

ረ) በግብርና ምርምር ተቋማትና የምርምር ውጤት ተጠቃሚዎች መካከል የጠነከረ ግንኙነት እንዲኖር የተለያዩ መድረኮችን ያዘጋጃል፤

ሰ) የግብርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ ከአገር ውስጥ የግብርና ምርምር ተቋማት ጋር ምርምርን በጋራ ማካሄድ ለሚፈልጉ የውጭ የምርምር ድርጅቶች የግብርና ምርምር ማካሄድ የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል፤ ይገመግማል፣ ፈቃድን ይሰርዛል፤

ሸ) የአገራዊ ግብርና ምርምር ሥርዓት አቅምን ለመገንባት በአገር ደረጃ ከውጭ አገራት ወይም ተቋማት ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን እና ፕሮጀክቶችን ያስተባብራል፣ ይመራል፤

ቀ) በግብርና ምርምር ሥርዓቱ አካላት የሚቀርቡ አገራዊ መረጃዎችን እና ሳይንሳዊ ጽሁፎችን ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

በ) የምክር ቤቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች ያከናውናል፤

ተ) የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

ቸ) ዓላማውን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

**፲፪.<u>የሴክሬታሪያቱ አቋም</u>**

፩/ሴክሬታሪያቱ:-

ሀ) በመንግሥት የሚመደብ ዋና አስተባባሪ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል አስተባባሪ፣

ለ) የምርምር ዘርፍ አስተባባሪዎች፣

ሐ) አስፈላጊው የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

excellence upon meeting the criteria;

f) organize various forums to establish strong bond between agricultural research institutions and research output consumers;

g) issue license for foreign research institutions intending to undertake agricultural research in partnership with national agricultural research institutions; evaluate and revoke license;

h) coordinate and lead relations and joint projects with foreign countries and institutions to build the capacity of national agricultural research system;

i) collect and organize national data and scientific publications generated by the agricultural research system and create conducive conditions for utilization of same;

j) perform day to day activities of the Council;

k) own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

l) Carry on such other activities necessary for the fulfillment of its objective.

**12. <u>Organization of the Secretariat</u>**

1/ The Secretariat shall have:

a) a Chief Coordinator and Deputy Coordinator to be assigned by the Government; and

b) research sector coordinators; and

c) the necessary technical and administrative support staffs.

፰ሺ፱፻፶

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚመደቡ አስተባባሪዎች በግብርና ምርምር ዘርፍ በቂ ልምድ እና አስፈላጊው የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡

2/ The Coordinators to be assigned pursuant to sub-article (1) of this Article shall have ample experience and necessary educational qualification in the field of agricultural research.

**፲፫. <u>የዋና አስተባባሪው ሥልጣንና ተግባር</u>**

፩/ የሴክሬታሪያቱ ዋና አስተባባሪ የሴክሬታሪያቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን ከምክር ቤቱ ሰብሳቢ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የሴክሬታሪያቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሴክሬታሪያቱ ዋና አስተባባሪ:-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ የተመለከቱ የሴክሬታሪያቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የሴክሬታሪያቱን ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ)የሴክሬታሪያቱን የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለሴክሬታሪያቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ እንዲደረግ ያዛል፤

ሠ) ሴክሬታሪያቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸዉ ግንኙነቶች ሁሉ ሴክሬታሪያቱን ይወክላል፤

ረ) የሴክሬታሪያቱን የሥራ ክንውንና የሒሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

፫/ የሴክሬታሪያቱ ዋና አስተባባሪ ለሴክሬታሪያቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሴክሬታሪያቱ ሠራተኞች በውክልና

**13.<u>Powers and Duties of the Chief Coordinator</u>**

1/ The Chief Coordinator of the Secretariat shall serve as Chief Executive Officer of the Secretariat and shall, subject to the general direction of the Council, direct and manage the day to day activities of the Secretariat.

2/ Without prejudice to the generality of sub-article (1) of this Article, the Chief Coordinator of the Secretariat shall:

a) exercise the powers and duties of the Secretariat stipulated under Article 11 of this Regulation;

b) employ and administer employees of the Secretariat in accordance with federal civil service laws;

c) prepare and submit to Council work plan and budget of the Secretariat and implement the same upon approval;

d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work plan of the Secretariat;

e) represent the Secretariat in its dealings with third parties;

f) prepare and submit performance and financial report of the Secretariat to the Council;

3/ The Chief Coordinator of the Secretariat may delegate part of his powers and duties to other employees of the Secretariat to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Secretariat.

ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡



**፲፬.<u>የምክትል አስተባባሪው ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክትል አስተባባሪው:-

፩ የሴክሬታሪያቱን ተግባራት በማቀድ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና አስተባባሪውን ያግዛል፤

፪/ በዋና አስተባባሪው ተለይቶ የሚሰጠውን ሥራ ያከናውናል፡፡

፫/ዋና አስተባባሪው በማይኖርበት ጊዜ ዋና አስተባባሪውን ተክቶ ይሰራል፡፡

**፲፭. <u>የሴክሬታሪያቱ በጀት</u>**

የሴክሬታሪያቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

**፲፮. <u>ስለ ሂሳብ መዝገብ</u>**

፩/ ሴክሬታሪያቱ የተሟላና ትክክል የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፤

፪ የሴክሬታሪያቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ሌሎች ኦዲተሮች ይመረመራሉ፡፡

**፲፯. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፲፬ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**14.<u>Powers and Duties of the Deputy Coordinator</u>**

The Deputy Coordinator shall:

1/ assist the Chief Coordinator in planning, organizing, directing and coordinating the activities of the Secretariat;

2/ perform other duties specifically assigned to him by the Chief Coordinator;

3/ act on behalf of the Chief Coordinator in his absence.

**15.<u>Budget of the Secretariat</u>**

The budget of the Secretariat shall be allocated by the Government.

**16. <u>Books of Accounts of the Secretariat</u>**

1/ The Secretariat shall keep complete and accurate books of accounts;

2/ The books of accounts and financial documents of the Secretariat shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor designated by him.

**17. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Addis Ababa, this 23rd day of March 2016**

**HILEMARIAM DESALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**